# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፣ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 85 ታህሳስ 22 2002 ዓ.ም

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

ወያኔ ሞት እና የእድሜ ልክ እስራትን የመሰሉ ከባድ ቅጣቶችን እንደምን በመናኛ ማስረጃ ተብየዎች ተንተርሶ ይፈርዳል? ለምንድነው ወያኔ ከግንቦት7 ጋር የተገናኙ ጉዳዮችን አምርሮ የሚይዘው? ወያኔ ለማንኛውም ተቃውሞ ምህረት የሌለው ቢሆንም ክፋቱ በግንቦት7 ላይ ለምንድነው የበረታው? የሚሉና የመሳሰሉ ጥያቄዎች ከየአቅጣጫው እየፈለቁ ናቸው። **ዝሩዝሩን ገጽ 2 ያንብቡ**

### የወያኔ አገዛዝ "ኤርትራ ተቃዋሚዎችን በሱዳን በኩል ሊታዘምትብኝ ነው ሲል" አምቆት የከረመውን ፍርሀቱን ይፋ አደረገ

የወያኔው የደህንነት ክፍል ሃላፊ ፣ ጌታቸው አሰፋ፣ ከትናንት በስቲያ ጀምሮ በመቀሌ ከተማ ውስጥ ሲካሄድ በነበረው የኢትዮ ሱዳን የኢኮኖሚና የዳርድንበር ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ለተገኙት የሱዳን ባለስልጣናት እንደተናገረው ፣ ኤርትራ የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎችን አስታጥቃ በሱዳን በኩል ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ ዝግጅት እያደረገች ነው ብሎአል። የደህንነነት ሃላፊው ሽብር ሲል የገለጸው የኢትዮጵያ ነጻ አውጭዎች እንቅስቃሴ ገና ከአሁኑ ወያኔን እንቅልፍ መንሳት መጀመሩን ራሱ ወያኔ ያመነ ሲሆን፣ በአካባቢው የሚደረገውን የተቃዋሚዎች እንቅስቃሴ የሱዳን መንግስት እንዲቆጣጠርለትም እጅግ ሰፊና ለም የሆነውን የአገራችንን መሬት ለሱዳን መንግስት በእጅ መንሻነት አሳልፎ ለመስጠት በርካታ ወገኖቻችንን ተወልደው ካደጉበት ቀዬ እያፈናቀለ መሆኑ በተለያየ ዜና አውታሮች ሲዘገብ መቆየቱ ይታወቃል። **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

### ወ/ት ብርቱካን በግፍ የታሰረችበት የመጀመሪያው አመት በአዲስ አበባና በተለያዩ የውጭ አገራት ከተሞች ታስቦ ዋለ

የፈላጭ ቆራጩ መለስ ዜናዊ አገዛዝ የነጻነት አርበኛ የሆነችውን ወ/ት ብርቱካንን ያሰረበት አንደኛ አመት በአንድነት ፓርቲ ጽህፈት ቤትና በተለያዩ የአለማችን ክፍሎች በሻማ ማብራትና በተለያዩ ዝግጅቶች መከበሩ ታውቋል። በአንድነት ጽ/ት ቤት ግቢ ውስጥ በተደረገው የሻማ ማብራት ስነስርአት በመቶዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ተገኝተው ለነጻነት አርበኛዋ ያላቸውን አድናቆትና ድጋፍ ገልጸዋል፤ እንድትፈታም ጥያቄ አቅርበዋል። በአሜሪካና በደቡብ አፍሪካ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንም የሻማ ማብራት ስነስርአት በማድረግ የወ/ት ብርቱካንን መፈታት ጠይቀዋል። በርካታ ድህረ ገጾችም ወ/ት ብርቱካንን የአመቱ ምርጥ ኢትዮጵያዊ አድርገው መርጠዋቸዋል።

**ወደ ገጽ 3 ዞሯል**

### የጂማ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ካለፈው ሰማንት ጀምሮ አድማ ላይ ናቸው፤ በአድማው የተሸበረው ወያኔ በአዲስ አበባና በሌሎች ቦታዎች ሰራዊቱን አስፈሯል

ባለፈው ሳምንት የተጀመረው የጅማ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ተቃውሞ አሁንም ድረስ እንደቀጠለ መሆኑን ሪፖርተራችን ከስፍረው ዘግቧል። ተማሪዎቹ የወያኔው አገዛዝ የወላጆቻቸውን የእርሻ መሬቶች እየቀማ ለአበባ እርሻ እንዲውሉ ማድረጉን በእጅጉ የተቃወሙ ሲሆን፣ እስካሁን ለውጭ አገር ባላህብቶች የተሰጡት መሬቶች ለወላጆቻቸው እንዲመለሱ ጠይቀዋል። ተማሪዎቹ በአሁኑ ጊዜ በአገሪቱ የሚታየውን የመሬት ሽያጭ አካሄድ ማውገዝ ብቻ ሳይሆን ፣ ሌሎችንም የመብትና የዲሞክራሲ ጥያቄዎች በማንሳት ላይ መሆናቸውን ሪፖርተራችን አክሎ ገልጿል።

ካለፈው ሳምንት ጀምሮ ተማሪዎቹ ትምህርት ያቆሙ ሲሆን፣ ከትግራይ ተወላጅ ጥቂት ካድሬዎች በስተቀር የሁሉም ብሄርና ብሄረሰብ ህዝቦች በአንድነት በመሆን አድማውን እያደረጉ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሎአል። የፌደራል ፖሊስና የክልል ፖሊስ አባላት ወደ ዩኒቨርስቲው ዘልቀው በመግባት ተማሪዎቹ ትምህርት እንዲጀምሩ ለማስፈራራትና የተለያዩ ሙከራዎችን ቢያደርጉም ተማሪዎቹ ግን አሁንም ባቋማቸው በመጽናት ተቃውሞዋቸውን በማድረግ ላይ ናቸው። የተማሪዎች ተቃውሞ እያየለ በመምጣቱም ጂማ በከፍተኛ ወታደራዊ ጥበቃ ስር እንደሆነች ዘጋቢያችን ገልጿል።

**ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

### የወያኔውን የእርዳታ አሰጣጥ ዘዴ የተቹና ለአለማቀፍ ድርጅቶች ያጋለጡ ገበሬዎች በመታሰር ላይ ናቸው

ወያኔ በረሀብ ለተጠቃው ወገናችን የተላከውን የእርዳታ እህል ለፖለቲካ ድጋፍ ማስገኛ ማዋሉን ተከትሎ አለማቀፍ ተቋውሞው እየጠነከረ በመጣበት ማግስት፣ ጉዳዩን ያጋለጡ ገበሬዎች በመታሰር ላይ መሆናቸውን ብሉም በርግ የተባለው ታዋቂ ድህረገጽ ዘግቧል።

ድህረገጹ ከትናንት በስቲያ ይፋ ባደረገው ዘገባ፣ ለአለማቀፍ የሰብአዊ መብት ድርጅቶች ምስክርነት ለመስጠት የተስማሙ ሰባት ገበሬዎች ህዳር 12፣ 2002 ዓም ተይዘው ታስረዋል። ለእስር የተዳረጉት ገበሬዎች የአረና ትግራይ ድርጅት አባላት ሲሆኑ፣ ወያኔ ለደህው ወገን የሚላከውን እህል ለፖለቲካ ድጋፍ ማስገኛ እንደሚያውለው ምስክርነታቸውን ለአለማቀፍ የሰብአዊ መብቶች ተከራካሪ ድርጅቶች ለመስጠት ወደ አዲስ አበባ ተጉዘው ነበር። ወያኔ ገበሬዎቹ ምስክርነታቸውን ለአለማቀፍ ድርጅቶች የሚሰጡ ከሆነ በአገር ክህዳት ወንጀል ተከሰው እስከ አርባ አመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እንደሚቀጡ እንዳስፈራራቸው ድጅረገጹ አክሎ ዘግቧል። **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

### የወያኔ ቁንጮዎች በፍትህ አካላቱ ላይ ቀጥተኛ ጣልቃገብነት እንዳላቸው አንድ ዲፕሎማት ገለጹ።

መለስ ዜናዊ በግንቦት 7 አባላትና በወታደራዊ መኮንኖች ላይ የተሰጠውን የይስሙላ ፍርድ በተመለከተ የሰጠው አስተያየት አገዛዙ በፍትህ አካላቱ ላይ ያለውን ቀጥተኛ ጣልቃገብነት ያሳያል ሲሉ አንድ ዲፕሎማት ገለፁ ።

ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉት እኝህ ዲፕሎማት ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጹት መለስ ዜናዊ ሰሞኑን ከጋዜጠኞች ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ በአገሪቱ ውስጥ ያለውን የፍርድ ቤት አሰራር በአንድ ግለሰብ ቁጥጥር ውስጥ መውደቁን ቁልጭ አደርጎ የሚያሳይ ነው ብለዋል። መለስ ዜናዊ በግንቦት 7 ተከሳሾች ላይ ለሞትና ለእድሜ ልክ እስራት የሚያበቃ በቂ መረጃ እንደነበረ ለመግለጽ "አሁን የተገኘው መረጃ ከአሁን ቀደም ለፍርድ ቤት ከቀረቡት ክሶች ሁሉ የማያወላዳ ነው" ማለቱ ተቃዋሚዎች በተደጋጋሚ ሲሉት እንደነበረው የፖለቲካ ባላንጣዎችን ለማጥፋት እስካሁን ለፍርድ ቤቱ ሲቀርቡ የነበሩ የፖለቲካ ነክ ክሶች በሙሉ መረጃ ያልነበራቸው የፈጠራ ውንጀላዎች መሆናቸውን ማመኑን ከማስገንዘቡም በላይ ወደ ፍርድ ቤት የሚመሩትን የፖለቲካ ክሶች በሙሉ እርሱና ጥቂት የወያኔ ቁንጮዎች የሚያቀነባብሩት መሆኑን ያመላክታል በማለት ዲፕሎማቱ አስረድተዋል። በግንቦት 7 ተከሳሾች ላይ ቀረቡ የተባሉት የሰነድ መስረጃዎች ብዛት ለስራው ለተመደቡት የወያኔ አቃቤ ህግና ዳኞች በሙሉ የሥራ ጊዜ ለመሸፈን ከ8ወራት በላይ መፍጀቱ እየተነገረ ተደራራቢ ሥራ ለያዘው የወያኔ ጠቅላይ ሚንስቴር እንዴት በብርሃን ፍጥነት እንደተዳሰሰና "የማያወላዳ ማስረጃ" ተደርጎ አንደታየ ገና ከክሱ አመሰራረት ግልጽ ነበር ያሉት እኚሁ ዲፕሎማት በአለማችን ካሉ አምባገነኖች ሁሉ እንደ ወያኔ የሚመራውን አገር ፍትህ ያዋረደ፤ ተቋማቱንም የፖለቲካ መጠቀሚያ መሳሪያ ያደረገ አንድም አገር በምድራችን ላይ የለም ብለዋል።

**ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

### በወያኔ አምባገነን አገዛዝ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ የማይታሰብ ነው ሲል የአፋር ህዝብ ፓርቲ አስታወቀ

ፓርቲው ከትናንት በስቲያ ባወጣው መግለጫ በወያኔው አምባገነንና ጨቋኝ አገዛዝ ውስጥ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ለማድረግ የሚያስችል ምንም አይነት የተመቻቸ ሁኔታ የለም ብሏል

ወያኔ ለ20 አመት ለሚሆን ጊዜ ህዝቡን እያታለለና እያጭበረበረ በስልጣን ላይ መቆየቱን የአስታወቀው የአፋር ህዝብ ፓርቲ በወያኔ የምርጫ ድራማ ውስጥ ገብቶ መሳተፍ የወያኔን እድሜ ከማርዘም ባለፈ ሌላ ፋይዳ ስለማይኖረው መራጩ ህዝብም ሆነ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫው መሳተፍ የለባቸውም ሲል ገልጿል

# ርእሰ አንቀጽ



## የሰሞኑ የእነ መለስ ውሳኔ የነገረን ቁም ነገር ወያኔን ለማስወገድ መፍጠን እንዳለብን ብቻ ነው!!!

ሰሞኑን እነ መለስ በግንቦት7 አመራር አባላትና በመከላከያ ሠራዊት፣ በፖሊስ እና በደህንነት ተቋማት ውስጥ የአንድን ዘውግ የበላይነት ለማንገስ ተብሎ የተዘረጋን ዘረኛ አደረጃጀት በይፋ በመቃወማቸው ምክንያት በመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ተሳትፈዋል ብለው በከሰሷቸው የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ላይ ያሳለፏቸው ጭካኔ የተሞላባቸው ውሳኔዎች ኢትዮጵያዊያንን ብቻ ሳይሆን የውጭ አገር ዜጎችንም እያነጋገረ ነው።

ወያኔ ሞት እና የእድሜ ልክ እስራትን የመሰሉ ከባድ ቅጣቶችን እንደምን በመናኛ ማስረጃ ተብየዎች ተንተርሶ ይፈርዳል? ለምንድነው ወያኔ ከግንቦት7 ጋር የተገናኙ ጉዳዮችን አምርሮ የሚይዘው? ወያኔ ለማንኛውም ተቃውሞ ምህረት የሌለው ቢሆንም ክፋቱ በግንቦት7 ላይ ለምንድነው የበረታው? የሚሉና የመሳሰሉ ጥያቄዎች ከየአቅጣጫው እየፈለቁ ናቸው። ወያኔ ግንቦት7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄን የሚፈራባቸው በቂ ምክንያቶች አሉት ብለን እናምናለን። በዚህም ምክንያት ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ተጠቅሞ መሪዎቹንና አባላቱን ቢያጠፋ ደስተኛ ነው። ወያኔ በቆየ መጠን የሚያደርሰው ጉዳት ከፍተኛ በመሆኑ በአስቸካይ ለመገላገል መረባረብ ያለብን መሆኑ እራሱ ወያኔ ሰሞኑን በሰጠው ውሳኔ አማካይነት ግልጽ አድርጎልናል። ለመሆኑ ለምንድነው ወያኔ ግንቦት7ን አጥብቆ የፈራው?

1. ግንቦት7 **<u>“ቅድሚያ፣ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ጉዳዮች”</u>** በሚለው የአመራር መርህ መሠረት ትኩረቱን ወደ አንድ አቅጣጫ ያሰባሰበ ድርጅት መሆኑ ወያኔን አስፈርቶታል። ኢትዮጵያ በርካታ ችግሮች የተደቀኑባት አገር መሆኗ እሙን ነው። ለችግሮቻችን መፍትሄ ሊሆኑ ይችላሉ ተብሎ የሚታሰቡ የተለያዩ የፓለቲካ፣ የአገር አስተዳደር፣ የኢኮኖሚ አስተሳሰቦች አሉ፤ ወደፊትም ይኖራሉ። ግንቦት7 በአሁኑ ሰዓት በፓሊሲና በርዕዮተዓለም ጉዳዮች ጎራ ከፍሎ በመከራከር ጊዜና ጉልበትን ከማጠፋት በቅድሚያ አገርን ማዳን እና መፍትሄ አለኝ ለሚል ወገን ሁሉ እድል የሚሰጥ የፓለቲካ መድረክ ማበጀት ይኖርብናል ብሎ ግልጽ የሆነ የአጭር ጊዜ ግብ ይዞ የተነሳ ድርጅት በመሆኑ ወያኔ በለመደው አጀንዳ የማስቀየር ዘዴው የሚፈታለት አልሆነም:: የግንቦት7 ግብ *ወያኔን አስወግዶ ሕዝብ መሪዎቹን በነፃነት የሚመርጥበት ሥርዓት መሠረት መገንባት ነው* በሚል ማጠቃለል ይቻላል። የመጀመሪያው ቀዳሚ ተግባራችን ወያኔን ማስወገድ ነው ብሎ ደምድሞ ተግባራዊ ሥራዎችን እየሠራ ነው። ይህ ከብዥታ የጠራ በወያኔ ማንቁርት ላይ ያነጣጠረ አቋም ቢያስበረግገው ሊደንቀን አይገባም።
2. ግንቦት7 ግልጽ የሆነ ግብ እና ሁሉንም ሰው ሊያሳትፍ የሚችል የትግል ስልትና አደረጃጀት ይዞ በመነሳቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ በርካታ አባላትና ደጋፊዎችን ማፍራቱ ወያኔን አስደንግጦታል። ከአነሳሱ ጀምሮ ግንቦት7 በተለያዩ መስኮች የዳበረ ልምድና ሙያ ባላቸው ሰዎች መገንባቱ፤ በወጣቶች ዘንድ ያለው ተቀባይነት እና በኢትዮጵያ ውስጥና ውጭ ያለው ተደማጭነት ከወያኔ ቅድመ–ስሌት ውጭ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ግንቦት7 ራሱ ወያኔ ውስጥ ሰርጎ በመግባቱ የወያኔ ቁንጮዎች የገዛ ጥላቸውን ጭምር እንዲጠራጠሩ አድርጓቸዋል። ይህም በአንድ ወገን ሥልጣን በጥቂት እጅግ በሚተማመኑ የአንድ መንደር ሰዎች እጅ ውስጥ እንዲገባ በማስገደድ ወያኔን ከድሮው የባሰ ዘረኛና ከራሱ ደጋፊዎቹም ሳይቀር የተነጠለ ሲያደርገው፤ በሌላ ወገን ደግሞ ቁጥር ያድን መስሎት መላውን ሕዝብ በአባልነት ለመመዝገብ የሚያደርገው ጥረት መላ ቅጡ የጠፋበት እንዲሆን አድርጎታል። የወያኔ የአባላት ምልመላ ጅምላነትና ልቅነት የግንቦት7 ህዋሳትን በወያኔ ድርጅት ውስጥ ማቋቋምን ቀላል ተግባር አድርጎታል። የእነዚህ ሁሉ ድምር ግንቦት7 ሩቅ ነው ሲሉት አጠገባቸው በመገኘት እረፍት ነስቷቸዋል።
3. ለዘመናት የኢትዮጵያ ፓለቲካ ልሂቃንን ሲያወዛግብ የቆየው የብሄራዊ አንድነት እና የብሄር/ብሄረሰብ መብቶች ጉዳይ በግንቦት7 ውስጥ ተቻቸለው በሚስተናገዱበት መጠን ረግበዋል። በአገር አቀፍም ሆነ በብሄር የተደራጁ ድርጅቶች ዓላማቸውን ለማሳካት የሚፈልጉበት ኢትዮጵያ የምትባል አገር መኖር ያለባት መሆኑ ለሁሉም ግልጽ እየሆነ ነው። ከዚያ ቀጥሎ ማንኛውም ድርጅት ዓላማውን መጫን ሳይሆን ለነፃ የሕዝብ ውሳኔ የሚገዛ እስከሆነ ድረስ ትግላችን የጋራ ነው። ይህም ከእለት እለት ግንዛቤ እያገኘ በመምጣት ላይ በመሆኑ ተቃዋሚዎችን እርስ በርስ በማጣላት የተካነው ወያኔ እዚህ መግቢያ ቀዳዳ አጥቶ ተቸግሯል።
4. የወያኔ የጦር ሠራዊትም ሆነ የስለላ ድርጅቱ ከውጭ ለሚያያቸው ጠንካራ ይምሰሉ እንጂ በዘረኝነትና በጥቅም በታወሩ ድውያን የሚመሩ ደካማ ተቋማት መሆናቸው እና በአንድ ምት የሚፈርሱ የእምቧይ ካቦች መሆናቸውን ከማንም በላይ ግንቦት7 የሚያውቅ መሆኑን ወያኔዎች ያውቃሉ። ስለሆነም ከመቀደም እንቅደም ቢሉ እውነታቸውን ነው።
5. በኢትዮጵያዊያን የተለመደ የፓለቲካ ጨዋነት ምክንያት ስለወያኔ ዘረኛ አደረጃጀት በግልጽ ሳይነገር ቆይቷል። ይህ ደግሞ ወያኔን እጅግ የጠቀመ ሲሆን በስሙ የሚነገድበት የትግራይ ሕዝብን ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ በተወሰነ መጠንም ቢሆን ነጥሎታል። ግንቦት7 ይህንን “አይነኬ” ግንብን በመነቅነቅ የወያኔን ዘረኝነት በማጋለጡ ዛሬ ወዳጆቹ የሆኑ መንግሥታት ዲፕሎማቶችም በአደባባይ የሚያነሱት ጉዳይ ሆኗል። በትግራይ ውስጥም የተቃውሞ ፓለቲካ ሥር እየሰደደ በመሆኑ ትግራይ የወያኔ ማስፈራሪያና መሸሸጊያ መሆኗ እያበቃለት ነው።

በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ወያኔ የግንቦት7 መሪዎችን፣ አባላትና ደጋፊዎችን ለማጥፋት መላውን ኃይሉን ቢጠቀም ሊደንቀን አይገባም። የሰሞኑን የወያኔ የሞትና የእድሜ ልክ እስር ውሳኔን ከዚህ አንፃር ስንረዳው አንገብጋቢው ጉዳይ በወያኔ መዳፍ ውስጥ የሚገኙትን ጅግኖች ነፃ ለማውጣት መጣደፍ ይሆናል።

በዚህም ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ የግንቦት7 አባላትና ደጋፊዎች የሰሞኑ የእነ መለስ ዜናዊ ውሳኔዎች ወያኔን ለማጥፋት የጀመርናቸውን እርምጃዎች እንድናፋጥን የሚያደርጉ የማንቂያ ደወል አድርገን እንድንወስዳቸው ያሻል። ዘግይተናል፤ ወያኔን በቶሎ ካልተገላገልን ጉዳቱ ከባድ ነው። በወያኔ ድርጅቶችና ጦር ሠራዊት ውስጥ ያላችሁ አገር ወዳዶች የውስጥ ትግላችሁን ከግንቦት7 ጋር በማቀናጀት ከሕሊና ወቀሳ የምትገላገሉበት ወቅት አሁን ነው። አለበዚያ ግን ለጥቅም ስትሉ ነፃነታችሁንና አገራችሁን አሳልፋችሁ ለወያኔ ሰጥታችኋልና የሕዝብ ቁጣ በእናንተም ላይ ይወርዳል። ወሳኙ ፍልሚያ ውስጥ ነን። የቻለ በግንባር ያልቻለ በደጀንነት ይሰለፍ። የሰሞኑ የእነ መለስ ዜናዊ ውሳኔ የነገረን ቁም ነገር ወያኔን ለማስወገድ መፍጠን እንዳለብን ነው። መልእክቱ ደርሶናል ታጥቀን እንነሳ!

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## የአውሮፓ ህብረት በግንቦት ሰባት አባላትና ወታደራዊ ምኮንኖች ላይ የተላለፈውን የሞት ውሳኔ አወገዘ

የአውሮፓ ህብርት የወያኔው ፍርድ ቤት በ5 የግንቦት 7 አባላትና ሲቪሎች ላይ የተላለፈውን የሞት ውሳኔ አውግዞ፣ የሞት ፍርድ በኢትዮጵያ እንዲቀር አጥብቆ ጠይቃል።የአውሮፓ ህብረት የወያኔው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ጭካኔ የተሞላበትና ሰባዊነት የጎደለው ነው ሲል ካውገዘ በሁዋላ፣ እርምጃው ሰዎችን ከድርጊታቸው የሚያግዳቸው ሳይሆን በኢትዮጳያ ውስጥ ያለውን የፍትህ ውርጃ የሚያሳይ ነው ብሎአል። በዚህ ውሳኔም ሊቅለበስና ሊተካ በማይችል ሁኔታ የሰዎች ህይወት ይጠፋል ብሎአል።

የሞት ቅጣት በመላው አውሮፓ የተወገዘ መሆኑን የጠቀሰው ህብረቱ፣ የሞት ቅጣት ይተግበር ከተባለ እንኳን ቢያንስ የተወሰኑ አለማቀፍ መስፈርቶች መሟላት ነበረባቸው ሲል የወያኔውን ፍርድ ቤት አካሄድ አውግዟል። የአውሮፓ ህብርት የኢትዮጵያ መንግስት የሞት ቅጣትን እንዲያወግዝ ጠይቆ፣ በግንቦት 7 አባላት ላይ የሞት ውሳኔው ተግባራዊ እንዳይሆን ጠይቀዋል።

የአውሮፓ ህብረት ያወጣው መግለጫ የወያኔውን የፍርድ ቤት አሰራር የሚያጋልጥ ብቻ ሳይሆን፣ በአገሪቱ ያለውን የፍትህ እጦት በመላ የሚዳሰሰ መሆኑን መግለጫውን የተከታተሉ አስትያየት ስጪዎች ተናግረዋል። ህብረቱ ያወጣው መግለጫ ከመቼውም ጊዜ በላይ ጠንካራ ሲሆን፣ አለማቀፍ ድርጅቶችና መንግስታት በወያኔ ድርጊት እየተማረሩ መምጣታችውን እንደሚያመለክትም አስረድተዋል።

በተያያዘ ዜናም የኢትዮጵያ ህዝባዊ አብዮትዊ ፓርቲ (ኢህአፓ) እንግልት እስራት፤ ስደትና ሞት የህውሃት/ ኢህአዴግ ጸረ ዲሞክራሲያዊነት አበይት መገለጫወች በሚል ረስ ባውጣው መግለጫ የወያኔው የይስሙላ ፍርድ ቤት የስጠውን ፍርድ በጽኑ አውግዟል ፓርቲው በመግለጫው “ቀደም ሲል ይደረግ እንደነበርው ሁሉ በአሁኑ ወቅትም በህወሃት /ኢህአዴግ ሙሉ ቁጥጥር ስር የሚገኘው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ታህሳስ 13 ቀን 2002 ዓ.ም ዋለ በተባለው ችሎት በግንቦት 7 ንቅናቄ የአመራር አባላት የጦር መኮነኖችና ሌሎችም ንጹሃን ኢትዮጵያውያን ዜጎች ላይ የሞትና የዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ፍርደ ገምድላዊ ብያኔ ስጥቶል ስለሆንም ኢሃፓ (ዲሞክራሲያዊ) ይህንን የሞትና የድሜ ልክ እስራት ፍርድ ገምድላዊ ብያኔ በጥብቅ ያውግዛል ብላአል”

ኢሃፓ “ህወሃት/ኢህአዴግ በተልይ በድህረ ምርጫ 97 ወቅት ያስችኳይ ጊዜ አዋጅ በማወጅና ቅልብ ነፍሰ ገዳዮችን በማስማራት በምላው የሃገሪት ዜጎች ላይ የደሰውን በድል፤ እልቂትና ጭፍጨፋ ታሪክ ይቅር የማይለው ፍጹም አረመኔያዊ ተግባር መሆኑን አስታውሶ በአሁኑ ወቅት ደግሞ ተቃዋሚውችን በማሳደድና በማሰር አዳክሞ እንደለመደው ራሱ ተወዳድሮ ራሱ በአሸናፊነት የሚወጣበትን መንገድ መርጧል” ብሷል

ስለዚህም ይላል ኢሃፓ ”እንግልት፤ እስራት፤ ስደትና ሞትን በቀጣይነት ማፋፋም ዋነኛ የፀር ዲሞክራሲያዊነቱ መገለጫ የሆነውን አምባገነን አገዛዝ አስወግዶ በነጻና ፍትሃዊ ምርጫ በኢትዮጵያ ህዝብ ይሁንታ ለሚመስረት ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት በጋራ መነሳት አማራጭ የሌለው ውቅታዊና ህዝባዊ ጥያቄ ነው”

**በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን**

**የፖስታሳጥን ቁጥር :-** POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# ፕሬዚዳንት ኦባማ ኦስሎ የኖቤል ሽልማት ስነስርአት ላይ ተገኝተው ያደረጉት ንግግር በግርድፉ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ እንደሚከተለው

**ቀርቦአል** **ክፍል 1**

ግርማዊነትዎ፣ ግርማዊ ቤተሰቦች፤ የተከበራችሁ የኖርዌይ የኖቤል ሽልማት ኮሚቴ አባላት፣ አሜሪካውያን እና በአለም ላይ የምትኖሩ ህዝቦች በሙሉ፡

ይህንን ሽልማት የምቀበለው ከጥልቅ አክብሮት እና ምስጋና ጋር ነው። ሽልማቱም የሚነግረን ስለ ታላቁና ዋነኛው ምኞታችን ሲሆን፤እኛም የዚች አለማችን ስቃይና መከራ የእጣ ፈንታ ምርኮኞች አለመሆናችንን ነው። በተግባር ላይ የምናዉላቸው ድርጊቶቻችንም ታሪክን ወደ ፍትሃዊ አቅጣጫ እነዲያመራ የማድረግ ወሳኝ ሚናን ይጫወታሉ።

ከዚህም ጋር በተያያዘ ይህ መልካም ዉሳኔአችሁ የፈጠረውን ቀላል የማይባል ውዝግብ መገንዛቤን ሳላወሳ ብቀር ግዴለሽ የሆንሁ ያህል ይሰማኛል። ውዝግቡ የተፈጠረበት ምክንያት በከፊል እጂግ ፈታኝ በሆነው የአለም መድረክ ፈታኝ ጉዞ መጀመሪያ እንጂ መጨረሻው ላይ ባለመሆኔ ነው። የዓለማችን ታላላቅ ባለታሪኮች ከሆኑትና ይህንን ሽልማት ከተቀበሉ እንደ ሽዌትዘር እና ኪንግ ፣ ማርሻል እና ማንዴላ ከመሳሰሉ ባለታሪኮች አንጻር ሲታይ፤ እስካሁን ድረስ እኔ ያከናወንሁዋቸው ተግባራት ኢምንት ናቸው። ይህም ሆኖ አሁንም በዓለማችን ፍትህን ለማግኘት በመጣራቸው እየተደበደቡና ለእስር እየተዳረጉ ያሉ ወንዶችና ሴቶች ፤ በረድኤት ድርጅቶች ዉስጥ ያሉና ሰዎችን ከሰቆቃ ለመታደግ በአድካሚ ስራ የተጠመዱ፤ ሌሎችም በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ትኩረትን ያላገኙ ነገር ግን በጀግንነትና ቅንነት በሚያከናውኗቸው ተግባራት ለአደገኛ ጨለምተኞች ሳይቀር ተስፋን የፈነጠቁ ይገኛሉ። በመሆኑም ይህ ሽልማት/ ክብር ከኔ ይልቅ ታዋቂ ለሆኑት፣ ወይም ደግሞ ከሚታደጉዋቸው ሰዎች በስተቀር በሌሎች ለማይታወቁቱ ለነዚህ ወንዶችና ሴቶች ሊሰጥ ይገባ ነበር ከሚሉት ጋር እኔ ለመከራከር አይቻለኝም ።

ነገር ግን ምናልባትም ይህንን ሽልማት ከመቀበሌ ጋር ተያይዞ በእጅጉ ትኩረት እንዲሰጠው ያደረገው ከሁለት ጦርነቶች ጋር የተፋጠጠችው ሃገር ዋናው የጦር አዛዥ የመሆኔ እውነታ ነው። ከነዚህ ጦርነቶች አንደኛው እየተጠናቀቀ ነው። ሌላኛው አሜሪካ የማትሻው ግጭት ሲሆን፤ ኖርዌይን ጨምሮ ሌሎች 42 ሃገራት የደገፉትና እኛን የተቀላቀሉበት አላማውም እራሳችንን እና ሌሎች አገሮችን ከተጨማሪ ጥቃት መከላከል የሆነው ጦርነት ነው።

አሁንም በጦርነት ውስጥ የምንገኝ ሲሆን በሺህ የሚቆጠሩ ወጣት አሜሪካውያን ራቅ ብሎ በሚገኝ ሃገር ለመዝመታቸውና ለሚያደርጉትም ውጊያ ተጠያቂውና ሃላፊውም እኔ ነኝ። ከእነኝህ አሜሪካዊያን ወታደሮች ውስጥ ግማሾቹ ሊገሉ ፤ ግማሾቹ ደግሞ ሊሞቱ ይችላሉ። በመሆኑም ወደዚህ የመጣሁት ጦርነት ምን ያህል ዋጋን ሊያስከፍል እንደሚችል እያሰብኩ፤ ብሎም በሰላም እና በጦርነት መካከል ባሉ ግንኙነቶች ላይ በሚነሱ አስቸጋሪ ጥያቄዎች እና እኛም አንደኛውን በሌላው ለመተካት እያደረግናቸው ባሉ ጥረቶች ዙሪያ ባሉ ሃሳቦች ተውጬ ነው።

እነዚህ ያነሳሁዋቸው ጥያቄዎች አዲስ አይደሉም። ጦርነት በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ከመጀመሪያው የሰው ልጅ ጋርም ተከስቶአል። ታሪክ ከጀመረበት ግዜ አንስቶ የጦርነት ሞራላዊነት ጥያቄ ውስጥ ገብቶ የማያውቅ ሲሆን፤ ልክ እንደ ድርቅ እና እንደ በሽታ ሁሉ ተጨባጭ እውነታ ነው፤ ጎሳዎች፣ ብሎም ዘመነኞቹ ስልጣንን ለመጨበጥ እና ልዩነቶቻቸውንም ለመፍታት የተጠቀሙበት መንገድ ነበር።

በዚህ ሂደትም ልክ ህጎች በተለያዩ ቡድኖች መካከል የሚነሳ አመጽን ለመቆጣጠር ታስበው እንደሚወጡት ሁሉ፤ ፈላስፎች፣ የእምነት እና የመንግስታት መሪዎች የጦርነትን አስከፊ ጥፋት የመቆጣጠር ጥረት አድርገዋል። በዚህም መልኩ "የፍትሃዊ ጦርነት" መርህ የተከሰተ ሲሆን ጦርነትም ፍትሃዊ ለመባል የሚያስችለው የተወሰኑ ሁኔታዎች የተሙዋሉ እንደሆነ ብቻ ከሚል እሳቤ እንደነበረ ያሳየናል። ይኸውም በጦርነት ወቅት ሌሎች አማራጮች ከተሙዋጠጡ እና እራስን ለመከላከል በሚደረግ ሂደት ውስጥ ሲኮን፤ የሀይል አጠቃቀምም ተመጣጣኝ በሆነበት ሁኔታና ፤ በተቻለ መጠንም ሲቪሉን ህብረተሰብ ለጥቃት በማያጋልጥ መልኩ መሆን እነደሚገባው ያስገነዝባል።

እርግጥ ነው ሁላችንም እንደምናውቀው በታሪክ ውስጥ በአብዛኛው የ"ፍትሃዊ ጦርነት" መርህ በቂ የሆነ ትኩረትን ሲያገኝ አልታየም።ልክ ከእኛ በመልክ የተለዩትን ወይም ከእኛ ለተለየ አምላክ የሚጸልዩት ላይ ምህረት የለሽ የመሆናችንን ያክል የሰው ልጆች አንዳቸው ሌላኛውን ለመግደል የሚያስችላቸውን አዳዲስ ስልቶችን የማሰብ አቅማቸው ማለቂያ የሌለው እንደሆነ ተረጋግጧል። በወታደሮች መካከል የሚደረጉ ጦርነቶች ታጣቂዎችን እና ሲቪሉን ህዝብ መለየት ወደማይቻልበት ወደለየለት አውዳሚ ጦርነትነት በመሸጋገር በመንግስታት መካከል ለሚደረጉ ጦርነቶች በር የከፈቱ ሆነው ታይተዋል። በቀጣዮቹ ሰላሳ አመታት ውስጥ እንደዚህ አይነት አሰቃቂ መጨራረስ ይህንን ዓለም በእጥፍ ሊቆጣጠር ይችላል። ሶስተኛው አምፓየር (የናዚ ጀርመኒ አገዛዝ መጠሪያ የነበረው) እና የአክሲስ ሀይሎችን (የናዚ ጀርመን፣ ኢጣልያንንና ጃፓን ፈጥረውት የነበረውን ህብረት) ከመጣል የበለጠ ፍትሃዊ የሆነ ጦርነትን ማሰብ ከባድ ሆኖ እንኩዋን፤ በሁለተኛው የአለም ጦርነት ሳቢያ በአጠቃላይ ካለቁት ወታደሮች ቁጥር ይልቅ ሕይወታቸውን ያጡት ሲቪሎች ቁጥር አጠቃላይ ድምር በልጦ የተገኘበት ግጭት ነበር።

ይህን ከመሰለ ጥፋት ማግስት እና የኒኩሊየር መሳሪያ መፈጠርን ተከትሎ ለአሸናፊዎችም ሆኑ ተሸናፊዎች መንግስታት ግልጽ እየሆነ የመጣው ጉዳይ ይህች አለም ሌላ የአለም ጦርነት እንዳይቀሰቀስ የሚከላከሉ ተቋዋማት እንደሚያስፈልጉዋት ነው።እናም የአሜሪካ ህግ መወሰኛ ምክር ቤት (ሰኔት) የሊግ ኦፍ ኔሽንስን ውድቅ ካደረገ ከሩብ ምእተ አመት በሁዋላ ለአሜሪካዊው ውድሮው ዊልሰን ይህንን ሽልማት እንዲቀበል ያስቻለውን ሃሳብ በማቅረቡ አሜሪካ በግምባር ቀደምትነት የዓለምን ሰላም ለመገንባት የሚያስችለውን ማለትም የማርሻል እቅድና የተባበሩት መንግስታትን፤ ወደጦርነት የሚያስገቡ ሁኔታዎችን ክትትልና ቁጥጥርን፤የሰባአዊ መብትን የማክበር ስምምነት፤ የዘር ማጥፋት ወንጀል የማስወገድን፤ የአደገኛ ጦር መሳሪያዎች ጥብቅ ቁጥጥር መሰረትና የግንባታ እቅድን ነድፋለች።

እነዚህ ጥረቶች በብዙ መንገዶች ተሳክተዋል። አዎን በጣም አስከፊ ጦርነቶች ተካሂደዋል፤ እልቂቶችም ተፈጽመዋል። ይሁን እንጅ ሶስተኛ የአለም ጦርነት ግን እስካሁን አልተካሄደም።ቀዝቃዛውም ጦርነት በደስታ በፈነጠዙ በርካታዎች ግንቡ ሲናድ አብሮ አክትሞአል። የንግድ ልውውጥ አብዛኛውን ዓለም አቀራርቦታል።በቢሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎችም ከድህነት አረንቋ እየወጡ ነው።ነጻነት እና የእራስን እድል በራስ መወሰን ፤ እኩልነት እና የህግ ልእልና የሚባሉት ሃሳቦች በከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሰዋል።እኛም ያለፉት ትውልዶች አይበገሬነትና አርቆ አስተዋይነት ወራሾች ከመሆናችንም በላይ የኔ የራሴም አገር በሚገባ የምትኮራበት ታሪክ ነው።

ይሁንና በአዲሱ ምእተ አመት ገና በመጀመሪያው አስርተ አመት ላይ ባለንበት ሁኔታ ይኸው ዘመናትን ያስቆጠረው የሰላም መሰረታችንና የግንባታ እቅዳችን አዳዲስ ጥቃቶች እየተፈታተኑት ነው፡፡ ዛሬ የሚታየው የአለም በሁለት የኑክሌር ጦር መሳሪያ ሃያላን ፍጥጫ ውስጥ መውደቅ ወደጦርነት ሊያመራ ይችላል የሚለው ስጋት ቀጣይነት ሊኖረው እንደማይችል የሚጠበቅ ቢሆንም የኑክሌር ሀይል የማመንጨት አደጋን ከፍ ሊያደርገው ይችላል። ሽብርተኝነት የረጅም ግዜ ታክቲክ ሆኖ ይቆይ እንጅ ፤ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ለጥቂት እብሪት ያሳበጣቸው እኩይ ሰዎች ንጹሃን ዜጎችን በጅምላ ለመፍጀት የሚያስችላቸውን እድል ይሰጣቸዋል።

ከዚህም ባለፈ መልኩ በሃገራት መካከል የሚደረግ ጦርነት በአገር ውስጥ ሊነሱ ለሚችሉ ጦርነቶችም በር እየከፈተ ነው። የጎሳ ወይም የእምነቶች ግጭቶች እንደገና ማንሰራራት፤ የመገንጠል ጥያቄ የሚያነሱ ቡድኖች መበራከት፤ ነጻ አውጪ ቡድኖች እና መንግሰት አልባ አገሮች መፈጠር፤ እነዚህ ሁሉ ክስተቶች ሲቪሉን ህብረተሰብ ማለቂያ ወደሌለው ትርምስ እየዳረጉት ነው። ዛሬ እየተካሄዱ ባሉት ጦርነቶች በጦርነቱ ከሚሳተፉት ወታደሮች ቁጥር የላቀ የሲቪሉ ህብረተሰብ እያለቀ ነው፤ ወደፊት ግጭትን ሊያስከትል የሚያስችል ዘር እየተዘራ ነው፤ ኢኮኖሚ ተቃውሷል፤ ሲቪሉ ህብረተሰብ ተከፋፍሏል፤ ህጻናት በብርቱ ተጎድተዋል።

ዛሬ እኔ ለጦርነት ፍጹም የሆነ መፍትሄን ይዤ አልቀረብሁም። የማውቀው ነገር ቢኖር ለነኝህ ፈታኝ የሆኑ ችግሮች መፍትሄ ሊሆን የሚችለው የጋራ ራእይ ሲኖረን፤ ጠንክረን መስራት ስንችልና ለአስርተ ዓመታት በአደባባይ እየታገሉ ያሉት ወንዶችና ሴቶች ትግል በቀጣይነት መዝለቅ ሲችሉ ነው። እንዲሁም ፍትሃዊ ለሆኑ ጦርነቶችና ገዥ ለሆነ ፍትሃዊ ሰላም አዳዲስ ዘዴዎችን ልናስብ ግድ ይለናል፡.

እውነቱን በመቀበል እንጀምር – ብጥብጥ ያለበት ቅራኔን በእኛ እድሜ ማስቀረት አንችልም። ለወደፊቱም ሕዝቦች – በግልም ሆነ በጋራ – ኃይልን መጠቀም አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ከሞራል አንፃርም ተገቢ የሚሆንበት ሁኔታ ይኖራል።

ይህንም ንግግር ሳደርግ ከዓመታት በፊት ማርቲን ሉተር ኪንግ ተመሳሳይ በሆነው የክብር ሽልማት ስነስርአት ላይ የተናገረዉን በማስታወስ ነው። "አመጽ ቋሚና ዘላቂ የሆነ ሰላምን አያመጣም። ምንም አይነት ማህበረሰባዊ ችግርንም አያቃልልም፤ እንዲያዉም የባሰዉን ዉስብስብ የሆኑ ችግሮች ያመጣል"። እንደ አንድ እዚህ የቆመ የሉተር ኪንግ የእድሜ ልክ የስራ ዉጤት የሆነ ሰው አመጽ ለሌለበት ትግል ሞራላዊ ሃይል የምስክርነት ቃሌን እሰጣለሁ። አውቃለሁ፡ በማህተመ ጋንዲ እምነትና ህይወት ምንም ነገር ፍጹም ደካማ አልመሆኑን፤ ፍጹም አድርባይ አለመሆኑን፤ ፍጹም የሆነ ቀጥተኛ አስተሳሰብ አለመኖሩን።

ነገር ግን እንደ አንድ አገሬን ከጥቃት ለመከላከል እና ለመመከት ቃል ኪዳን የገባ መሪ፤ በነሱ አርአያነት ብቻ ለመመራት አልችልም። የዓለማችንን ችግር ባለበት ሁኔታ እጋፈጣለሁ፤ እንዲሁም ለአሜሪካዊያን ደህንነት አስጊ የሆኑ ችግሮችን ለመጋፈጥ ብቻየን አልቆምም። አንሳሳት! ክፉት በዓለም ላይ አለ። ሰላማዊ ትግል ሂትለርን ሊገታው አልቻለም ነበር። ድርድር የአልቃይዳን መሪዎች መሣሪያዎቻቸውን እንዲጥሉ አያደርግም። አንዳንዴ ጉልበት መጠቀም ያስፈልጋል ማለት ከሃቅ የራቀ ምፀት አይደለም፤ ይልቁንስ ታሪክን በቅጡ መረዳት፤ የሰውን ልጅ ድክመቶችን ማወቅ እና የምክንያታዊነት ውስንነትን መገንዘብ ነው።

ይህንን ጉዳይ ያነሳሁት፣ በዚህም ጉዳይ የጀመርኩት ምክንያቱ በብዙ አገሮች ውስጥ ለማንኛውም አላማ ቢሆን ወታደራዊ ሃይልን በአሁኑ ግዜ መጠቀምን አስመልክቶ የተደበላለቁ አስተያየቶች ስለሚነሱ ነው ። አንዳንዴም ይኸው ስሜት በአለም በወታደራዊ ሀይል ተወዳዳሪ የሌላትን አሜሪካንን በጥርጣሬ ከመመልከትም ጋር የሚያያዝም ሆኖአል።

ነገር ግን ዓለም ሊያስታውስ የግድ የሚለው በቀላሉ የምናያቸው ዓለም ዓቀፍ ተቋማት- ስምምነትና ድርድርም ብቻም አይደለም- ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ያለውን መረጋጋትን ያመጣልን። ምንም አይነት ስህተት ይሰራ፡ እውነታው የሚከተለው ነው፤ የተባበሩት የአሜሪካን መንግስት ባለፉት ስድስት አስርተ ዓመታት ጊዚያቶች በዓሜሪካዊያን ደምና ወታደራዊ ጥንካሬ የዓለማችን ደህንነት እንዲጠበቅ ርዳታዉን አድርጓል። ይህም የአሜሪካዊያን ወንዶችና ሴቶች ወታደራዊ አገልግሎትና መስዋዕትነት፡ ሰላምና ደህንነትን ከጀርመን እስከ ኮሪያ እንዲሁም ዲሞክራሲያዊ ስራአትን እንደ ባልካን ባሉ ሃገራት ላይ እንዲሰፍን አድርጓል።

**ክፍል 2 በሚቀጥለው ሳምንት ይቀጥላል**

## የወያኔ አገዛዝ "ኤርትራ ተቃዋሚዎችን በሱዳን በኩል ሊታዘምትብኝ. ..

ከገጽ 1 የዞረ

በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ እየተቀጣጠለ ባለው ህዝባዊ ተቃውሞ እየተደናገጠ የመጣው ወያኔ፣ ለረጅም ዘመናት በሱዳን ውስጥ በስደት የሚኖሩት ኢትዮጵያዊያን ሳይቀሩ ተላልፈው እንዲሰጡት ለሱዳን መንግስት በይፋ ጥያቄ ማቅረቡም ታውቋል። በመልካም አስተዳደር እጦት ምክንያት አገራችን ለዘመናት የተነፈገቿውን ፍትህ፤ እኩልነትና ነጻነት በሰላማዊ የምርጫ ህግ ለማምጣት ራዕይ ሰንቀው የተነሱትን የሰላም ታጋዮች "ስልጣን ከእጄ ፈልቂቃችሁ ለማውጣት ከፈለጋችሁ ጫካ ግቡና ሞክሩኝ" ሲል ይደነፋ የነበረው ወያኔ፤ "ነጋ ጠባ አገር ሰላም ነው ብሎ በሚደስኩርበት ምድር እንዲህ በአንድ ጊዜ ምን አይቶ በቁም የሚያቃዠ ፍርሀት ውስጥ እንደገባ ለብዙዎች እንቆቅልሽ ሆኖአል። እንደ አንዳንድ ውስጥ አዋቂ ምንጮቻችን መረጃ ወያኔን ከፉኛ ያስደነገጠው፤ በመከላከያ ሠራዊቱ ውስጥ በሰፈነው ዘረኛ አስተዳደር ምክንያት እንደሰደድ እሳት እየተቀጣጠለ በመጣው ብሶት ከአሁን ቦኋላ የአገዛዙን እድሜ ለማራዘም የህይወት መስዋዕትነት ሊያስከፍል በሚችል ግዳጅ ተሰማርቶ ሊሞትላቸው የሚችል የሚተማመኑበት ጦር እንደሌለ ከመገንዘብ የተፈጠረ ጭንቀት ነው ። ከዚህም በተጨማሪ በሰራዊቱ አካባቢና በሲቪሉ ህብረተሰብ ውስጥ የሚታየው ህዝባዊ ተቃውሞ እየተጠናከረ መምጣት ወያኔን ተስፋ እንዲቆርጥ ማድረጉን አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች ይናገራሉ።

በተያያዘ ዜናም ወያኔ ለስልጣን እድሜው ማርዘሚያ ሲል ፣ አባቶቻችን በደማቸው ያቆዩትን መሬት ለሱዳን አሳልፎ ለመስጠት የሚያደርገውን እንቅስቃሴ የትግራይ ህዝብ በስብሰባው አዳራሽ በመገኘት ተቃውሞውን ማሰማት እንደሚኖርበት ያነጋገርናቸው ሰዎች ገልጸዋል። "ኢትዮጵያን ለመከፋፈል በጋራ ትብብር ስም ዱለታው በመቀሌ ሲካሄድ የትግራይ ህዝብ ዝም ብሎ ሊመለከት አይገባም፣ አባቶቹ በደምና በአጥንታቸው ያቆዩትን አገር ቆርሰው ለመስጠት ልጆቹ ሲስማሙ ሀይ ሊላቸው ይገባል" ሲሉ አስተያየት ሰጪዎች አክለዋል።

## ወ/ት ብርቱካን በግፍ የታሰረችበት የመጀመሪያው አመት . . .

ከገጽ 1 የዞረ

ወ/ት ብርቱካንን በማስታወስ በአዲስ አበባ መስቀል አደባባይ ሊደረግ የነበረው የሻማ ማብራት ስነስርአት በፖሊስ አባላት እንደተከለከለና የወ/ት ብርቱካን ምስል ያለበትን ቲሸርት ለብሰው ፊርማዎችን ሲያሰባስቡ የነበሩ ወጣቶች ታፍሰው መታሰራቸው ታውቋል። ገዛሀኝ ምትኩ፣ አሳምነው ብርሀኑ፣ ዘገየ እሸቴ፣ ቅድስት በቀለ፣ ናቲ መኮንንና ፋራህ አብደላ የተባሉ ወጣቶች ተይዘው መታሰራቸውን ኢትዮጵያ ሚዲያ የተባለው ድህረ ገጽ ዘግቧል።

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ያለው የዲሞክራሲና የፖለቲካ መብቶች ሙሉ በሙሉ በመታፈናቸው ፣ ህብረተሰቡ ሃሳቡንና ፍላጎቱን ለመግለጽ ከማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል። አንድ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ አስተያየት ሰጪ እንደተናገሩት ወያኔ በህዝቡ ላይ የሚፈጽመው ግፍ ና በደል ልኩን አልፏል፤ የህዝቡ መልስ ግን ገና ልኩን አላለፈም። የህዘቡ ስሜት ልኩን ሲያልፍ የሚያደርሰው ጉዳት ተወዳዳሪ የለውም ብለዋል።

## የጂማ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ካለፈው ሰማንት ... ከገጽ 1 የዞረ

በጂማ የተነሳው ተቃውሞ ወደ ሌሎች ዩኒቨርሰቲዎች ሊዛመት ይችላል ብሎ የፈራው ወያኔ የደህንነት ሰራተኞችን፣ የመከላከያና የፌደራል ፖሊሰ አባላትን በተያዩ ከተሞች ማስፈሩ ታውቋል። ባለፈው ሰኞ አዲስ አበባ ከወትሮው በተለየ በከፍተኛ ወታደራዊ ጥበቃ ስር እንደነበረች ያስታወሰው ሪፖርተራችን፣ ምክንያቱ ግልጽ ባልሆነ ሁኔታ ወታደሮች ሰዎችን ሲፈትሹ፣ ትኩር ብለው ሲያዩና የተለያዩ ወታደራዊ እንቅስቃሴዎችን ሲያደርጉ መመልከቱን ገልጿል። አንዳንድ ሰዎች እንደለመዱት ቦምብ ለማፈንዳት እየተዘጋጁ ይሆናል የሚል አስተያየት የሰጡ ሲሆን ሌሎች ግን የተለመደው ፍርሀታቸው መገለጫ ነው ሲሉ ጉዳዩን አጣጥለውታል። ሪፖርተራችን እንደገለጸው ከሆነ ግን ወታደራዊ እንቅስቃሴው በጂማ ዩኒቨርሰቲ የተነሳው ተቃውሞ በሌሎች ዩኒቨርሰቲዎችም ሊቀጣጠል ይችላል ከሚል ፍርሀት የመጣ ነው።

ቀኑንና ሌሊቱን በፍርሀት የሚያሳልፈው ወያኔ፣ ተቃውሞ ሊነሳ ይችላል ብሎ በሚያስብበበት ጊዜ ሁሉ ወታደሮችን ልኮ ህዝቡን እንደሚያሸብር የሚታወቅ ሲሆን፣ ሰሞኑን የሚታየው መደናገጥም የዚህ ውጤት ሊሆን እንደሚችል ብዙዎች ይስማማሉ። ከግንቦት 97 ምርጫ በሁዋላ በኢትዮጵያ የተነሱትን ተቃውሞዎች በሀይል ለማፈን የሞከረው ወያኔ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አገራዊ ተቃውሞች እንደገና ሊቀሰቀሱ ይችላሉ ብሎ እጅግ በመስጋቱ ወታደራዊ ሀላፊዎችን እየሰበሰበ ቁጥጥሩን እንዲያጠናክሩ እያደረገ ነው።

በቅርቡ የወያኔው አገዛዝ በአዲስ አበባ የሽብር ጥቃት ሊፈጸም ይችላል ብሎ ለአለማቀፍ ድርጅቶች ያስተላለፈውን ሰርኩላር ይፋ ማድረጋችን ከታወቀ በሁዋላ ከፍተኛ ሀፍረት ውስጥ የገባው ወያኔ፣ ሌሎች የሽብር ጥቃቶችን እያቀደ እንደሚገኝም ታውቋል። ምናልባትም በቅርቡ ፍንዳታዎች ወይም ሌሎች የሽብር ጥቃቶች በአገዛዙ የደህንነት ሰዎች ሊፈጸም እንደሚችል ያገኘነው መረጃ ጠቁሟል። ህብረተሰቡ በወያኔ የሽብር ጥቃት ሳይደናገጥ በወያኔ ላይ ያለውን ተቃውሞ ማጠንከር እንዳለበት መረጃውን የላኩን የደህንነት ሰዎች አክለው ገልጸዋል።

የዘረኛውና አምባገነኑ መለስ አገዛዝ ህዝቡ በሚያሳየው ውስጣዊ ተቃውሞ በእጅጉ እየተረበሸ በመምጣቱ ፣ ሰዎችን በማሰርና ሀሰተኛ ክሶችን በመክሰስ ለማስፈራራት ሙከራ እያደረገ መሆኑን በግንቦት 7 እና በሌሎች ወታደራዊ መኮንኖች ላይ የተመሰረተው ክስ ያሳያል።

## የወያኔውን የእርዳታ አሰጣጥ ዘዴ የተቹና ..... ከገጽ 1 የዞረ

የወያኔው አገዛዝ ሙሉ በሙሉ የተነጠቀውን ህዝባዊ ድጋፍ መልሶ ለማግኘት ሲል ህዝቡን በምግብ ለመደለል የሚያደርገው ሙከራ ኢሰብአዊ ብቻ ሳይሆን ወንጀልም ነው ሲሉ አንድ የህግ ባለሙያ ተናግረዋል። የዘር ፍጅት ማለት አንድን ወገን በዘር ወይም በፖለቲካ አመለካከቱ ወይም በእምነትና በመሳሰሉት ምክንያቶች ጨርሶ እንዲጠፋ ማድረግ ነው የሚሉት ምሁሩ ፣ ወያኔ እርሱን ያልደገፉ ሰዎችን በርሀብ እንዲያልቁ መፍረዱ ከዘር ፍጅት ተነጥሎ አይታይም ብለዋል። "ሰዎቹ ምግብ ከተከለከሉ በረሀብ እንደሚያልቁ ግልጽ ነው፣ ምግብ የሚከለከሉት ደግሞ የወያኔ ደጋፊ ስላልሆኑ ወይም የተቃዋሚ አባላት በመሆናቸው ነው፤ ይህ ግልጽ የሆነ ወንጀል ነው፤ በአለማቀፍ ፍርድቤትም የሚያስጠይቅ ነው"ብለዋል።

የውጭ አገር መንግስታት እንዲህ አይነት ግልጽ የሆነ ወንጀል ሲፈጠር እየተመለከቱ ጉዳዩን አጥብቀው አለመግፋታቸው ብዙዎችን ያበሳጨ መሆኑንም የሚደርሱን መረጃዎች ይጠቁማሉ። በውጭ አገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ድርጊቱን አጥብቀው በማውገዝ፣ አለማቀፍ አቋም እንዲያዝ ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው የህግ ባለሙያው አክለው ገልጸዋል።

## የወያኔ ቁንጮዎች በፍትህ አካላቱ ላይ ቀጥተኛ .... ከገጽ 1 የዞረ

ከምረጫ ዘጠና 97 በሁዋላ የተከሰሱት የቅንጅት አመራሮች፣ በተለያየ ጊዜ እየታሰሩ ዘብጥያ የሚወረወሩ የኦነግ ተጠርጣሪዎች እና ሌሎችም በፖለቲካ ምክንያት የታሰሩ ሰዎች በሚያወላዳ ማስረጃ ይፈረድባቸው እንደ ነበር አምባገነኑ መለስ ሳያውቀው ለማመን ተገዷል። ባልተሟላ መረጃ ውሳኔ ተሰጧቸው በእስር የሚማቅቁት እነ ወ/ት ብርቱካን ሚደቂሳና ሌሎችም የፖለቲካ እስረኞች በዚህ ንግግር ብቻ ነጻ መውጣት ይችሉ ነበር የሚሉት ዲፕሎማቱ፣ ሆኖም ግን መለስ እንደፈቀደው ከሚያዛቸውና ከሚቆጣጠራቸው ፍርድ ቤት ተብየ ተቋማት ፍትህ ስለማይጠበቅ መለስ በአደባባይ የሰጠው ምስክርነት ምናልባትም ለሌሎች ተቃዋሚዎች" የሚያድናችሁ የለምና አርፋችሁ የምንላችሁን አድርጉ" ለማለት በፍርሃት ለማሸመድመድ የታሰበ ነው አለያም እየተጠናከረ በመጣው ተቃውሞ ተደናግጦ መቀባጠር መጀመሩ ነው ብለዋል።

መለስ ዜናዊ ክሱን ከሽብርተኝነት ጋር ያያያዘው ከአሜሪካና ከአውሮፓ ድጋፍ ለማግኘት አስቦ መሆኑን የተናገሩት ዲፕሎማቱ ይህ ዘዴ ግን አስቀድሞ የተበላ እቁብ በመሆኑ ሊሰራ አይችልም ብለዋል። ጉዳዩ ከፖለቲካ ጋር እንዳይያያዝ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ የነበረው መለስ ፣ የአውሮፓ ህብረት የወቅቱ ፕሬዚዳንት የኢትዮጵያን የፍርድ ቤት አካሄድ ተችተው አስተያየት ከሰጡ በሁዋላ በእጅጉ መበሳጨቱም ታውቋል። በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ፍርድቤቶች በአንድ ሰው ቁጥጥር ስር መዋላቸውን በሁሉም ህዝቦች ዘንድ እየታወቀ በመምጣቱ የማሳመን ችግር የገጠመው መለስ ዜናዊ፣ በውጭ አገር የሚገኙ የግንቦት 7 አመራሮች ተላልፈው እንዲሰጡ ሲያደርግ የነበረው ጥረት ራሱኑ መልሶ እየመታው በመሆኑ ጥረቱን ለማቋረጥ እንደተገደደ ለማወቅ ተችሎአል።

መለስ በእስርቤት ውስጥ ያለውን ችግር በተለመደ ቅጥፈቱ ለመካድ የሞከረ ሲሆን፣ በተለይ በእነ ብ/ል ጄኔራል አሳምነው፣ በእነ ብ/ጄ ተፈራ ማሞና በሌሎችም እስረኞች ላይ የደረሰውን ድብደባ ድራማ ነው ብሎ ማጣጣሉ ብዙዎችን አበሳጭቷል። እንዲህ አይነት አይን ያወጣ ቅጥፈት ከአንድ ተራ ሰው እንኳን እንደማይጠበቅ አስተያየት ሰጪዎች ተናግረው፣ መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያ ህዝብ በግልጽ የሚያውቀውን ጉዳይ ሽምጥጥ አድርጎ መካዱ የግለሰቡን ማንነት ይበልጥ ከማጋለጥ ውጭ ሌላ ፋይዳ የለውም ተብሎአል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

በ7530 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ9610 KHZ በ31 ሜትር ባንድ ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።**

g7radio@ginbot7.org